# የህውሃተት አይን ያወጣ ዝርፊይ

ከመለስ ሸዋ(ኖርዌይ)

መቼም ጉድ ሳይሰማ የሃገሬ ሰው ውሎ አያድርም ከስም ውጪ ይህ ነው የሚባል የመወሰን ስልጣን ሳይኖራቸው የተለያየ እንግዳችንን በመቀበልና በመሸኘት የአለፉት አስራ ሁለት አመታትን በቤተ-መንግስት ያሳለፉት እርዕሰ ብሔር የመቶ አለቃ ግርማ ወ/ጎርጊስ ለስም ብቻ ይዘውት የነበረው የስልጣን ዘመናቸው መጠናቀቁን ተከትሎ ከቤተ-መንግስት ሲወጡ የሚገቡበት ቤት መንግስት መከራየት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ሆኖም በዚህ መጠን  በውድ ዋጋ መከራየቱ ስርዓቱ ምን ያህል በምዝበራ ገንዳ ውስጥ እየዋኘ እንዳለና ተራው፣ የተገፋው፣ የተናቀው፣ ሕዝብ የለት ጉርሱን መሸፈን አቅቶት የቆሻሻ ገንዳ ላይ ቀለቡን በሚፈልግበት በአሁኑ ሰዓት የስርዓቱ ሰወች በምዝበራ  የገነቡትን ህንፃ በእጅ አዙር በዚህ መጠን አከራዩተው ሲከብሩበት በዛ ሕዝብ ላይ ያላቸው ንቀትና ጥላቻን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ የዘረፋ ስልት ነው፡፡

በመሰረቱ  የወያኔ ህውሃት  ስርዓት፡ ስርዓት ከተባለ ከመጀመሪያው አንስቶ (ከምስረታው አንስቶ)ሀገር ማዋረድ፣ ቤሄራዊ ጥቅምን አሳልፎ መስጠት፣ በዙዎች የተሰዉለትንና  ለሶስት ሺ ዘመን ታፍራና ተከብራ የኖረች ሀገርን  ባህልና ቅርስን ማጥፋት (መመዝበር) ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ነገር ሁሉ በመዝረፍና ማግበስበስ ያኔ ጠዋት በእድሜያቸው  መጀመሪያ የተነሱለት የማይሰንፉበት  አላማቸው ነው፡፡

ከደደቢት ጀምሮ የተነሰለትን ሃገር የማፍረስና የመናድ እቅዶቸውን ለመተግበር እንደ  መነሻ የወሰዱት እርምጃ በወቅቱ የህዝብና የሃገር ሃብት  የሆኑት ባንኮችን መዝረፍ፣ በመቀጠልም እስካሁን በስሙ በሚነገድበት  በትግራይ ህዝብ  ርሃብና  ሰቆቃ ላይ በመንተራሰ ለርሃብተኛው የመጣውን እርዳታ በመዝረፍ  ኪሳቸውን እንዳደለቡ  ይህንን የጥፋት ቡድን  ሲመሰረት አበረው የነበሩ አስረድተውናል፡፡ ላለፉት ሃያ ሁለት አመታት የሃገርና የህዝብን ሃብት እያግበሰበሰ የኖረው የህውሃት ቡድን የሚፈጥራቸው የሙብት እረገጣዎችንም ሆኑ የሚያጠፏቸው የንፅሃን ዜጎች ህይወት መንስኤው ሃገር በመሸጥ ያግበሰበሱትን ሃብት ለማስጠበቅ ካላቸው ፍላጎት አኳያም ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሃገር የሚመራ ቡድን የተመሰረተበት አካባቢን በመለየት የንግድና የልማት ተጠቃሚ ማድረግ ከመሰረቱ በእብሪትና በማን አለብኝነት ላይ ለመመስረቱ ማሳያ ነው፡፡

በተለያየ ግዜ የሰርዓቱ አባላት የሚነግሩንና የሚደሰኩሩልን የኤኮኖሚ እድገት በዙሪያቸው ላሉ አፍቃሪ ህውሃት ብቻ እንጂ ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል እንዳልሆነ  ህዝብ የሚመራው ከድህነት በታች የሆነ ኑሮ በዚህም ምክኒያት በሃገሩ የመኖር ዋስትና በማጣት ከሃገር በመኮብለል የጎረቤት ሃገራትን እስር ቤት ማጨናነቁና በበረሃ እንዲሁም በባህር መበላቱ  የየቀን ክስተት መሆኑ አለ የሚባለው የኤኮኖሚ እድገት ጥቂቶች ያውም የስርዓቱ ሎሌዎች ብቻ ያበለፀገ ለመሆኑ እማኝ መጥቀስ አያሻውም፡፡

በትግራይ ህዝብ ስም ተሰይሞ የወያኔ ህውሃት ባለስልጣናት ባለ ድርሻ የሆነው ኢፈርት ስላለው ካፒታልም ሆነ አመታዊ ገቢው ምን ያህል እንደሆነ ህዝቡ የማወቅ እድል ባይሰጠውም እነኚሁ የስርዓቱ ሰዎች ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል ፍፁም በመናቅና ለክብሩ ቁብ ሳይኖራቸው በአገኙት አጋጣሚ ይህንን የሃገሪቷን አጠቃላይ የንግድ እንቅስቃሴ በሞኖፖል የተቆጣጣረውንና የንግዱን የህብረተሰብ ክፍል ከገበያ ውጪ ያደረገ  ከሃገርና ከህዝብ በተዘረፈ ገንዘብ የተመሰረተውን ኢፈርት አሁን ስላለበት ግዝፈትና ደረጃ በድፍረት ያወራሉ፡፡

ኤፈርት ያሉት ቁልፍ የንግድ ተቋማት መሰቦ ሲሚንቶ፣ መስፍን ኢንዱስትሪያል፣ ባባ ዳይሜንሽናል ስቶን፣ ሱር ኮንስትራክሽን፣ ኤክስፐረስ ትራንዚት፣ትራንስ ኢትዮጲያ፣አዲስ ፋርማሲዩቲክ፣ ጉና ትሬጊንግ፣ ሂወት አግሪካቸር፣ሼባ ታነሪ፣ ኤክስፔሪየንስ ኢትዮጲያ፣አልመዳ ጨርቃ ጨርቅና ኢዛና ወ.ዘ.ተ. . . . . . . ግምቱ 50 ቢሊየን ካፒታል ያለው ኤፈርት በነዚሁ የህውሃት ሰወች የሚመራ ነው፡፡

የነስብአት ነጋ ኢፈርት ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ከወያኔ ህውሃት በሚያገኘው ፖለቲካዊና ወለድ የለሽ የብድር አገልግሎት በመታገዝ የመንግስት የግንባታ እቅዶችን ያለተቀናቃኝ በመውሰድ የሌሎችን የግል ባለሃብቶችን ከውድድሩ እያወጣቸው መሆኑ በግልፅ የሚታይ እውነት ነው፡፡ በሃገሪቱ ውስጥ ለሚገነቡ ትላልቅ ተቋማት በምርት አቅርቦትም ሆነ በግንባታ በቀጥታ ያለ ጫረታ በመግባት ምዝበራውን በስፋት ተያይዞታል፡፡ ለምሳሌ መስፍን ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ከሶስት የስኳር ፋብሪካዎች የ2.6 ቢሊዮን ብር ኮንትራት መውሰዱ፣ መሰቦ ሲሚንቶ የአባይ ግድብ ግንባታን እንዲሁም የግቤ ሶስትን ግንባታ የሲሚንቶ አቅርቦታ ያለ ተቀናቃኝ መውሰዳቸው ባለድርሻ የሆኑት የህውሃት ሰዎች ከመቼውም በበለጠ ምዝበራው ላይ እየተጉ መሆኑን ያሳየናል፡፡

ብቻ ትልልቆቹ የህውሃት ሰዎች ከኢፈርት በተጨማሪም የግል ሃብት ሲያደራጁና ሲያሸሹ ሲከርሙ ትንንሽ ሎሌዎቻቸው እንዳቅማቸው ያቺን ሃገር ሲመዘብሩዋት አመታት ተቆጥረዋል፡፡

ባሳለፍነው አስቸጋሪ ዘመነ ህውሃት ይህ እኩይ ስርዓት ብዙ ገድሏል፣ ብዙ አስሯል የብዙዎችን ቤተሰብ አፍርሷል፣ ብዙዎችን ለአገርና ለህዝብ ትልቅ ስራ ሊሰሩ የሚችሉ ውድ የሃገር ልጆችን በልቷዋል፣ አሳዷዋል፡፡ በሃገራችን በሰላም የመኖር ህገ-መንግስታዊ መብታችንን እንዲሁም ሰው በመሆናችን ብቻ ሊኖረን የሚገባውን ሰዋዊ መብታችንን ጥሰው፣ የኛ የሆነውን ሁሉ ዘርፍውና ሃገር ሸጠው ያካበቱትን ንብረት ለማስጠበቅ በተቃራኒው ስለ ሃገርና ህዝብ ክብር፣ ነፃነት ያገባኛል ብለው የሚሟገቱ ለምሳሌ እነ እስክንድር ነጋ፣ አንዷለም አራጌ፣ በቀለ ገርባ፣ ኦልባና ሌሊሳ፣ መምህርት እሪዎት አለሙና የመሳሰሉት የህሊና እስረኞችን በፈጠራ ክስ ማጎሪያ ከተዋቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በሁሉም መስክ እጃቸው እረዝሞ በእምነት ተቋማት፣ በሞያ ማህበራት፣ እንዲሁም በየትኛውም የህዝብ አደረጃጀት ውስጥ በመግባት ሁሉም ቦታ ሁሉም ጥግ ደርሶ የሰላም አማራጮችን በሙሉ በመዝጋት በሃይል የበላይነቱን ለማስጠበቅ ዘረኛው ብድን ቀን ከሌት እየሰራ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ እንደመነሻ የጠቀስኩት በአዛውንቱ የሙቶ አለቃ ግርማ ወልደጎርጊስ ምክኒያት የሚሰበሰበው የሕዝብ ገንዘብ ማሳያ ሆነ እንጂ እንዲሁ ለሕዝብ ይፋ ሳይወጣ ቀርቶ በየክልሉ በዚህ ዘረኛ የወያኔ ቡድን ሃገር እንደ ስጋ ስትመተር አመታት አልፈዋል፡፡ ሆኖም ድርጊቱን በመኮነን ብቻ የምናልፈው ሳይሆን በቁርጠኝነት ልንታገለው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ለአስተያየት. melina.shewa19@gmail.com